# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

Tel 202 291 4217 mailling address: P.O.Box 73337, Washington Dc 20011


በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በነሐሴ 9 ቀን 2009 ዓም የተላለፈ ሐተታ

## መሪዎቹን የማያውቅ ሕዝብ ፤ ሕዝቡን የማያውቁ መሪዎች !

በሀገራችን የቅርብ ጊዜ የፖለቲካ ታሪክ ላይ ብቻ ስናተኩር፤ የተፈራረቁት መሪዎች ሁሉ፤ ሕዝባቸውን በሚገባ ሳያውቁ፤ ሕዝቡም እነርሱን ሳያውቃቸው፤ ሕዝቡ እየተገዛ፤ እነርሱም እየገዙ ማለፋቸውን መረዳት ይቻላል። ሕዝቡን ሳያውቁት ሥልጣን ይዘው፤ ሳይረዱት ገዝተው፤ ሳይወዱት -ሳይወዳቸው፤ ሳያቀርቡት- ሸሽቷቸው፤ ተኮራርፈውና ተቀያይመው ይለያያሉ። ሳይተዋወቁ የኖሩ በመሆናቸው.፤ባዕዳን እንጅ የአንድ ሀገር ዜጎች ሳይሆኑ ይቆያሉ። " የማያውቁት ሀገር እንደማይናፍቅ " ሁሉ ፤ እነርሱም በሚገባ ባለመተዋወቃቸው ምክንያት በሚለያዩበት ጊዜ መነፋፈቃቸው ቀርቶ፤ እንዲያውም **"እንኳን ተላቀቅን"** ብለው፤ ዳግመኛ እንዳይገናኙ ተማምለው ተነጣጠለው ይለያያሉ ።

ዳግመኛም መልሰው እንዳይታያዩ ይፈጣጠማል። የዚኽ ሁሉ ከስተት መጨረሻው፤ የሀገር መና ሆኖ መቅረት ይሆናል ። ሕዝቡም፤ የመሪ ያለህ! የሰብሳቢ ያለህ! እያለ ጩኸቱን ይቀጥላል ! አዲስ የሚመጣውም ቢሆን፤ ካለፈው ታሪክ ለመማር አይፈልግም ። በመሆኑም፤ የሀገሪቱ የቅርብ ጊዜ የፖለቲካ ታሪክ፤ እምቧለሌ እየተሽከረከረ ቆይቷል። ከዚኽ አዙሪት መውጣት አልተቻለም ። ከዚኽ ሽክርክሪት ሰብሮ መውጣት ካልተቻለ፤ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዕጣ -ፈንታ በፅልመት-ዳፍንት እየተደናበረ መቆየትን ይቀጥላል።

ያላወቁትንና ሊያውቁትም የማይፈልጉትን ሕዝብ በሚገባ ሳይረዱ፤ ለመግዛት ሲባል ብቻ የመንግሥት ሥልጥን መጨበጥ፤ በሀገራችን የተለመደ ክሥተት እያሆነ እስካሁን ድረስ ዘልቋል። ሕዝቡም፤ ያላወቁትና ያልተረዱት ሰዎች ብቅ ጥልቅ እያሉ፤ ተከስተው በመሰወራቸው፤አውላላ ሜዳ ላይ ተንገዋሎ ይቀራል ። ሀገሪቱም፤ ተቆርቋሪ ሕዝቡም ተንከባካቢ አጥተው ፤ አይዞህ፤ አይዞሽ ባይ ሳያገኙ፤ ለአልፎ -ሃጂ መንገደኛ መጫወቻ ይሆናሉ።

ዛሬ በሀገራችን ፤ገበሬው ጠፍቶ፤ በሬዎቹ ሥራ ፈትተዋል። ማሳውም ጦም አድሯል። ሀገሩም በርሃብ ተፈትቷል። መፅዋዕት ሰጭውም ተሰላችቷል። ሽማግሌ አዛውንቱም ከሳዳቸው ጎብጧል ። ጎበዛዝቱም ክንዳቸው ዝሏል ። ምዕመኑም ድምፁን አድፍጧል ። ሰኔንና ሰኞን ይጠብቃል። ወጣቱም ራዕይ አጥቶ ተቸግሯል ። ከሀገር ተሰድዷል። በየምድረ-በዳው ያሞራ ሲሳይ ሆኖ ቀርቷል። በሊቢያ በርሃ በአረመኒዎቹ ሠይፍ አንገቱ ተቀልቶ ቀርቷል። የዚኽ መሠረታዊው ምክንያትም ፤ሕዝቡን የሚያውቅ፤ ዜጎቹም እርሱን የሚያውቁት አገዛዝ ባላመኖሩ ነው። የቅርብ ጊዜ መሪዎች፤ እንዲያው ከናካቴው የሕዝቡን ማንነትና ምንነት ሳያውቁት ይገዙታል ቢባል የተጋነነ ነው ማለት የሚቻል አይመስለንም ። ሁኔታው ዕቅጩን ይመሰክራልና!

ለዚህ አባባል ሁለት በቂ ዋቢ -ምስክሮች መጥቀስ ተችሏል።

<u>**አንደኛው :----**</u>

ከአስራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድት/ 1966 ዓም ጀምሮ ለአስራ ሰባት ዐመታት የቆየው፤ ወታደራዊ አምባገንን አገዛዝ ነበር። ሀገሪቱንና ሕዝቧን በሚገባ አውቆ ሳይረዳ፤ ከወታደር ሠፈሩ ወጥቶ ፤ የደርግ ሶሻሊዝም፤ የኢትዮጵያ ሶሻሊዝም ፤ የታንዛንያ ሶሻሊዝም፤ የሩሲያ ሶሻሊዝም እያለ ተወናብዶ በማወናበድ ሀገሪቱን ምስቅልቅሏን አውጥቷት በወግ በማረጉ ሳይሰናበተ፤ ተወገደ ። የሚገዛውን ሕዝብ ሳያውቀውና ለማወቅም ጥረት ሳያደርግ መና ሆኖ እንደ ጉም በንኖ ጠፋ። በሙያና በስልጠና፤ የወታደር መለዮ የለበሰ ቢመስልም፤ እንደ ወታደር ግን ወታደራዊ ስልትና ስትራተጅ ወይም ዕቅድ ሳይኖረው፤ ሀገሪቱን ለሌላ አጥቂ አሳልፎ ሰጥቶ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ።

በስልታዊ ማፈግፈግ(Tactical Retreat ) እና በስትራተጂያዊ መከላከል ( Strategic Defense ) ያለውን ልዩነትና ተደጋጋፊነት ፤ ሊኖር የሚገባውን ወታደራዊ ጥበብና ክኅሎት ሳይኖረው በመቅረቱ የተኩስ አቁም ትዕዛዝ አስተላልፎ የተዋጊውን ሠራዊት ቅስም ሰበረ። እያፈገፈጉ መከላከል፤ እየተከላከሉ መጠናከር፤ እየተጠናከሩ መልሶ ማጥቃት፤ እያጠቁ ጠላትን መደምሰስ (Offensive- Defensive Strategy ) ሊይዝ ሲገባ፤ እንዲያው ጭራሹን የደጀኑን ጦር አጋልጦ መሸሽ፤ የነመንግሥቱ ና ተባባሪዎቹ አምሳ አለቃዎቹ ሙያ ነበር። ባንፃሩ ግን የኢትዮጵያን ሕፃናት፤ ሴቶችና አዛውንትን ይረሽኑ ነበር ። በወቅቱ፤ በሀገራችን የወረደውን ዘመነ- ፍዳ ፤ዛሬም በወያኔዎቹ እየተደገመ ነው።

ከወታደራዊ ጥንካሬ በመነሳት ወደ ሰላም ስምምነት ክብ ጠረጴዛ መሄድ ሲገባ፤ ትጥቁን ፈትቶ ጀሌውን ቀርቦ፤ ለአሜሪካኖች ለእነ ሄርማን ኮኸን ተንበርክኮ እጁን ሰጠ። ይኸ ድርጊት፤ ገናና ታሪክ ለአስመዘገበው ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሞት ሞት ነበር። የዛሬው ትውልድ የተረከበው ይኸንን አሳፋሪና ቅስም-ሰባሪ ታሪክ በመሆኑ፤ እንደ እግር እሣት ያንገበግበናል ። **ይኸንን ጥቁር ነጥብ ሳያዩ ያሸለቡት ሠማዕታት ምንኛ የታደሉ ናቸው?**

የጀግኖች ሞት ያስቀናል እንጅ ፤አያስለቅስም ! ለዚች አይዞሽ ባይ ለአጣች ሀገር፤ እየደጋገሙ ቢሰውላት፤ አይበዛባትም ! አዳዲስ ሠማዕታትም ይተካሉ እንጅ ተሰውረው አይቀሩም። የወያኔዎቹ አስቸኳይ ዐዋጅ መደንገግና ዐዋጁንም ማንሣት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የትግል ዐላማ አያሰናክለውም። ጊዜያዊ እፎይታ ያገኙ መስሏቸው፤ ትንሽ ሊተነፍሱ ይችሉ ይሆናል ! ምን ጊዜም ቢሆን ዕሣት ይዳፈን እንደሁ እንጅ ፤ ጨርሶ አይጠፋም ! " **ማነው እሳት ጠፋ ያለ የተጃጃለ ! " ያለውን** የገሞራዎን ግጥም ያስታውሷል !

ያ ከሠሃራ አፍሪካ በታች በትጥቅና በውጊያ ችሎታ ተወደዳዳሪ አልነበረውም የሚባልለት መከላከያ ሠራዊት እዳልሆነ ሆኖ እንዲቀር የተደረገው፤ ጠንካራ አመራር በማጣቱ ነበር እንጅ ፤ የተዋጊው ኃይል ድክመት እንዳልነበረ ሁሉም ያውቀዋል ። ይኸንንም የሻብዕያ መሪዎች፤ እያንገፈገፋቸውም ቢሆን ሳይወድዱ በግድ ይቀበሉታል ። ምን ጊዜም ቢሆን፤ ማነኛውም ሠራዊት ሊጠቃ የሚችለበት ምክንያት፤ በመሪዎቹ ድክመት እንጅ በተዋጊው ወታደር ድክመት እንዳልሆነ፤ የጦርነት ታሪክ

በተደጋጋሚ ያረጋገጠ ሀቅ ነው ። ከሻዕቢያና አሜሪካ ጋር ተመሳጥረው ጦሩን የፈቱት ያደከሙትንም የመንረሳቸው አይደሉም።

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ የማይተዋወቁ መሪዎችና ዜጎች የሚኖሩባት ሀገር ሆናለች። የሚተዋወቁ መሪዎችና ሕዝብ እንዲገናኙ ለማድረግ፤ ሰኔና ሰኞ እስኪገጣጠሙ ድረስ መቆየት አይገባም። " አምላክ ያመጠውን ፤አምላክ እስኪመልሰው" እያሉ መቆየት፤ የወያኔን ዕድሜ ሊያሳጥረው የሚችል አይደለም። "ልመና ሳሉ በቁመና ! " እንደሚባለው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ የአምላኩን ርዳታና ድጋፍ ሊያገኝ የሚችለው፤ እየኖረ ሲኖር እንጅ፤ እየሞተ ሲሞት አይደለም። " ሙታንን ሙታን ይቀብሯቸዋል " እንጅ ፤ ሕያው የሆነው የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ በህይወት እያለ ሀገሩ ስትጠፋ ዝም ብሎ ሊያይ አይገባውም። በዘመናት የሚፈራረቀው ትውልድ ሁሉ የየራሱን ኃላፊነት መወጣት መቻል አለበት እንጅ፤ ዕዳና ሸክም እርሱን ለሚተካው ትውልድ ማስተላለፍ የለበትም።

ያ ትውልድ ፤ ተወቀሰም ተመሰገነ፤ የራሱን ድርሻ በመሥዋዕት ከፍሎ ሄዷል ! ታሪክ ይፍረድበትም፤ ይፍረድለትም! ሀገሩ ኢትዮጵያ ግን ለዘለዓለም በነፃነት እንደምትኖር ብዥታ አይኖረውም !

ደካሞች እንጅ፤ ጠንካራ መሪዎች የሌሏት ሀገር መሆኗን የተገነዘቡት ገንጣይና አስገንጣይ ቡድኖች ፤ዓላማቸውን እንዲሙቱ ደርግ ዕድሉን ሰጣቸው። በጅግኖቹ ኢትዮጵያን ጦር ሜዳ ዳንኪራ እንዲጨፍሩ በሩን ከፍቶ ለቀቀላቸው። ሀገሪቱ ከፍተኛ ዋጋ ከፍላ ያሰለጠነቻቸውና ሰፊ ልምድና ተመክሮ ያካበቱትን ጀኔራሎችና ብቁ የጦር መሪዎቿን እየረሻነ፤ በሚያሳፍሩ የፖለቲካ ካድሬዎች ተክቶ ያን ጀግና ሠራዊት በተኖት ቀረ።

ይኸንን ሁሉ ለማስታወስ የምንገደደው፤ ያለፈውን ቁስላችንን ለመቅረፍ ሳይሆን፤ ወጣቱ ትውልድ ዕውነተኛውን የሀገሩን ታሪክ በሚገባ ተረድቶ፤ ወደፊት ሀገሪቱን የሚረከቡ ዜጎች ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን በሚገባ አውቀውና ተገንዝበው እንዲዘጋጁ ፍላጎት ስለአለን ነው። በግድ፤ ሀገራችን፤ መሪዎችና ዜጎች በሚገባ ተዋውቀው የሚኖሩባት ምድር ልትሆን ይገባል !

ደርግ፤ የሀገርን ነፃነት ጠብቆ፤ የሕዝብ አንድነት ሊያቆይ የሚችል ተግባር አከናውኖ ቢሆን ኖሮ፤ አምባገነንነቱ በመጠኑ ቢሆን እንኳ ፤ከታሪክ ወቀሳ ሊያቀልልት የሚችል ሁኔታ ያተርፍ ነበር። ፍርሃትና ድንቁርና የተላበሰ ስለነበር፤ ደርግ፤ የትውልድን ሚዛናዊ ብያኔ እንኳን ሳያገኝ ቀረ። በታሪክ ሂደት፤ አያሌ አምባገነን መሪዎች መጥተው ሄደዋል ። ሁሉም የታሪክ ፍርድ ብያኔ ተቀባይና የማያመልጡም ናቸው።

**<u>ሁለተኛው:</u>**

ደርግን ተክቼ መጣሁ የሚለው ወያኔና ተበባሪዎቹ ናቸው። ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የማወቅ ፍላጎቱም ችሎታውም ሳይኖራቸው፤ ባለውለታቸው የሆነው ደርግ ጥሎላቸው የሄደውን ቤተመንግሥት ሰተት ብለው ገብተው የማያውቁትን

ሀገርና የሚጠሉትንም ሕዝብ እየቀጠቀጡ የሚገዙበትን ዕድል እንዲያገኙ ሆነ። እንኳንስ መላውን ሀገርና ሕዝቧን ማወቃቸው ይቅርና ፤ ነፃ እናወጣዋለን የሚሉትን የትግራይን ሕዝብም ቢሆን ሊያውቁት የሚገባውን ያኽል አያውቁትም። የትግራይን ሕዝብ ከወገኑ ከቀሪው ኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ አያውቁትም። " እኳ ካባሃትኹም ፤ ካብ ወርቂ ሕዝቢ ተፈጠርና ! " ( እንኳን ከናንተ ከወርቂ ሕዝብ ተፈጠርን ) እያሉ በኢትዮያዊነቱ ኮርቶ የኖረውን የትግራይን ሕዝብ ሊያታልሉት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። የትግራይ ሕዝብ ወርቅነቱ የሚደምቀው፤ የሚያብበውና የሚያንፀባረቀው በኢትዮጵያዊነቱ ብቻ ነው። ይኽን ሃቅ ደግሞ ማንም ሳይነግረው፤ እርሱ ባለቤቱ፤ የትግራይ ሕዝብ በሚገባ አውቆት በአንድነቱ- በነፃነቱ ኮርቶ ኖሯል። ወደፊትም ይቀጥላል። ለዚህ ደግሞ፤ ወኪልና ቀላጤ የሚያስፈልገው ሕዝብ አይደለም።

ደርግ በማያቀውና ባልተዘጋጀበት ሁኔታ፤ በማያውቀው ሕዝብ ላይ በጫነው የባዕድ ርዕዮት ምክንያት፤ ያን ሁሉ ጥፋት አጥፍቶ እንደጠፋ ሁሉ፤ ወያኔም የደርግን ፈለግ በመከተል፤በማያውቃት ሀገርና በሚጠላው ሕዝብ ላይ፤በብሄር ነፃ አውጭነት ስም ተዘርዝሮ በማያበቃ ወንጀልና ጥፋት ሀገሪቱን እያመሳት ይገኛል፡፡

ምንም እንኳን ወያኔና ሻዕብያ፤ በኢትዮጵያ ጠላትነታቸው ያንድ ስንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸው ባይካድም፤ ሁለቱም በዘረጉት ያገዝዝ ሥርዓት ተፃራሪ አቋሞች ይከተላሉ።

ወያኔ፤ አንድ የነበረችዋን ሀገር እንዳልነበረች አድርጓታል ። ዜጎቿንም በቋንቋ፤ በነገድ ፤ በዘርና በሃይማኖት፤ በክልልና -ጎጥ ከፋፍሏቸዋል። ተገነጣጥለው እንዲለያዩ የሚያስገድድ ህጎች ጭኖባቸዋል። ሀገሪቱ የነበራትን የቆዳ ስፋት አጨማትሮታል ። ዳር እንበሯንም አስደፍሮታል ። ሰፋፊ- ቃዳ መሬቶቿን፤ ለባዕዳን አስረክቦባታል ። ኢትዮጵያዊነት እያከሰመ፤ ጎጠኝነት እንዲንሳራራ ተግቶ ይሰራል ። ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት አሳፋሪ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፤ የሚያሸማቅቅና የሚያገልል እያሆነ መጥቷል፤ ዛሬ በወያኔ !

ይኽ እንዳለ ሆኖ ፤ ወደ ፊት፤ ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን በሚገባ የሚያውቁ መሪዎች ሲመጡ የኢትዮጵያ ሁኔታ መሠረታዊ በሆነ መልኩ አዎንታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ መጠራጠር አይቻልም። ይኽ ግን በበጎ ምኞት ብቻ አይመጣም። ኢትዮጵያን እናድናት ብሎ የተሰለፈው ኃይል ጎልቶ መሳፍርት ከሌላው ስብስባና ክርክር ራሱን አላቅቆ በተጨባጭ አምራቂ ተግባር መፈፀም አለበት ።ያ ካልሆነ "ውሾቹ ይጮኻሉ ፤ ግመሎቹም የሄዳሉ ! " በማለት ወያኔዎቹ እያፌዙ እንዲቀጥሉ መፍቀድ ነው። ይኽ እንዲሆን ፤ እኛ አንፈቅድም። ይኽ እንዳይሆን ከሚፈልጉ ጋር ግን እንተባበራለን ! ዝባዝንኬ ወሬና ንትርኩ አብቅቶ ኢትዮጵያን በሚበጅና በሚጠቅም የህብረት ጥረትና ሂደት ሁላችንም እንድናገኝ ፍላጎታችንና ጥሪያችን ነው።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ጸረ ወያኔ ትግል !!